## 3. አርስ አደረ ተማምና ሥራውን እንዴት ያከሄዱ?

### 3. 1. የኒካራጉዋ ምሳሌ፣

አቶ ሚሼል ሜርሌ
ፓሪስ ፈረንሳይ

40 ዓመት የቆየውን የሶሞዛን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ገርስሰው በ1979 ዓ.ም. ሳንዲኒስቶች በኒካራጉዋ ስልጣን ሲይዙ የገጠሩን ችግር ለመፍታትም ሆነ ከገበሬዎች ጋር የሠመረ ግንኙነት ለመፍጠር ብዙ ችግሮች አጋጥመዋቸዋል፡፡ ትግል በሚያካሄዱበት ወቅት በገበሬው አካባቢ እምብዛም የተተከሉ አልነበረም፡፡ ስለሆነም ሳንዲኒስቶች ስለገበሬው የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ ሚና የነበራቸው ግንዛቤ በጣም የተሳሳተ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ከ1979ዓ.ም. ጀምሮ የተከተሉት የእርሻ ፖሊሲ ከመነሻው የተሳሳተ ፖሊሲ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ኒካራጉዋ ከጥቂት ክፍለዘመናት በፊት በስፔኖች በቅኝ ግዛትነት ስትያዝ ሁለት የተለያዩ ህብረተሰቦች ነበሯት፡፡ በአትላንቲክ ውቅያኖስ በኩል ያለው ክፍል እድገም እድገት ያላሳየና መደብ የለሽ ህብረተሰብ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በፖሲፊክ ውቅያኖስ በኩል ያለው በመጠኑም ቢሆን የተራመደና የተወሳሰቡ ማህበራዊ ግንኙነቶች ያሉበት ህብረተሰብ ነበር፡፡

ቅኝ አገዛዝ ሲመጣ ነባሩ ህዝብ እንዳለ ተፈጀ፡፡ 500 ሺህ ያህል ይገመት የነበረው የህዝብ ቁጥር ወደ ጥቂት ደርዘን ሺዎች ወረደ፡፡ በቀረውም ህዝብ ላይ አፖርታይድ በመሰለ ሥርዓት የሚሠራ የጭቆና የምዝበራ ቀንበር ተጫነበት፡፡

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ በነበሩ ህንዳዊ ህዝብ ትናንሽ መንደሮችና በቅኝ ገዥዎች በተያዙ ታላላቅ እርሻዎች መሃከል ትልቅ ልዩነት እየተፈጠረ መጣ፡፡ በነዚህ ሁለት ዓለሞች መሀከል ቀስ በቀስ በተለይ የክልሶች የገበሬ ኃይል እየተፈጠረ ሄደ፡፡ በቅኝ ገዥዎች ላይ እየተቀሰቀሰ የሄደውን የአርበኝነት ትግል የመራውም ይህ ክፍል ነው፡፡ ሃገሪቱም ነጻ ከወጣች በኋላ ጄኔራል ሳንዲኖ ሳካሄዱት ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገው ይኸ ክፍል ነው፡፡

የእርሻውን ፖሊሲ በሚመለከት የዚህ ክፍል ተቃውሞ የገዥው መደብ ማስፋፋት የሚመከረውን በኤክስፖርት ምርት /በተለይ በቡና ላይ/ ያተኮረውን ያመራር ሥልት ነበር፡፡

ሰንዲኒስቶች ሥልጣን ሲይዙ በፖስፊክ ውቅያኖስ በኩል ያለው እርሻ በጣም ዘመናዊ ነበር፡፡ ነገር ግን ለሃገሩ ህዝብ ምርት የሚያቀርቡት ሌሎች አካባቢዎች በጣም ወደኋላ የቀሩ ነበሩ፡፡ ቀደም ባሉት ዓመታት ሃገሪቱ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ገብታ ስለነበር ገዥው መደብ በጣም ተከፋፍሎ ነበር፡፡

በውጭ ገበያ ላይ ያተኮረው እርሻ በተለይ በዓለም ገበያ የቡና የጥጥ ዋጋ ከፍተኛ እስከነበረበት ወቅት ብዙም ችግር አልነበረበት፡፡ በኋላ ግን ዋጋ ማሽቆልቆል ጀመረ፡፡ ግን ሳንዲኒስቶች ፖሊሲ ሲያወጡ ይኸንን ቀውስ በሚገባ አልተገነዘቡም ነበር፡፡ ዘመናዊ እርሻዎችን በሰፊው ለማስፋፋት የሚጥር ፖሊሲ አወጡ፡፡ የከተሞችን ህዝብ ድጋፍ ለማግኘት ከገጠር በርካሽ እየገዙ እርካሽ እህል ማቅረብ ጀመሩ፡፡

ይህ ሁኔታ በተለይ በገጠር ተቃውሞዎችን ቀሰቀሰ:: ሳንዲኒስቶች ለዚህ ተቃውሞ ተገቢ መልስ መስጠት አቃታቸው የመሬት ይዞታ ማሻሻያ አዋጅ ሲወጣ ዓላማው የአገር ኢንዱስትሪውን ክፍል ዘመናዊ ለማድረግ ታስቦ ነበር:: ከታላላቅ ባለመሬቶች የተወረሱትን እርሻዎች ለገበሬው ከማከፋፈል ፋንታ የመንግሥት ወይም የህብረት እርሻዎች አረጓቸው:: የሀገሪቱ በጀት ትናንሽ ገበሬዎችን ከመርዳት ይልቅ ለትላልቅ የእርሻ ፕሮጀክቶች መዋል ጀመረ::

እርግጥ የአሜሪካኖች የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተጽእኖ እየጨመረ ሲሄድ፣ ሳንዲኒስቶች ይሸገን ፖለቲካቸውን ለማለስለስ ተገደዱ:: በተለይ ደግሞ ገበሬው በገፍ ወደ ተቃዋሚዎች ኮንትራዎች መሄድ ሲጀምር ስህተታቸውን መገንዘብ ጀመሩ::

እነዚህ ስህተቶች ብዙ ነበሩ:: ለከተሞች እርካሽ እህል ለማቅረብ ሲባል በእርሻ ምርት ንግድ ቁጥጥር ማድረግ ከነዚህ ስህተቶች አንዱ ነበር:: ያስገኘውም ውጤት የጥቁር ገበያ መዳበርን እንጂ የትናንሽ ገበሬዎችን ምርት ማዳበር አልነበረም:: በዚህ የተነሳ አብዮት ካስገናቸው ጥቅሞች በትክክል ለሁሉም አልተዳረሱም::

ከኒካራጉዋ ልምድ ሁለት ትምህርቶችን መቅሰም ይቻላል:: በመጀመሪያ፣ በረዥም ጊዜ ተቓምን ለመቀየር የሚጥር ፖሊሲንና በአጭር ጊዜ ለጊዜው ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት መወሰድ ያለባቸውን ፖሊሲዎች ማምታታት አደገኛ ነው:: ሁለተኛ ደግሞ፣ የመሬት ይዞታ ማሻሻያ ፖሊሲ ሊሳካ የሚችለው ገና ከመነሻው የገጠሩን ዓለም በሚያውቁት ሰዎችና በዚያ አካባቢ ላለው ህዝብ ችግሮች መፍትሄ ሲሰጥ፣ እንደዚሁም ደግሞ ይህንን ፖሊሲ አብረው የሚቀይሱና ህዝቡ እንዲቀበላቸው የሚያስችሉ የራሱ የገበሬው ድርጅቶች ሲኖሩ ብቻ ነው::

## 2. የአፍጋኒስታን ምሳሌ፣
ወይዘር ፔሬ /ፓሪስ ፈረንሳይ/

የአፍጋኒስታን ሁኔታ እንዲገባን አስቀድመን የሃገሪቱን የጂኦግራፊ አቀማመጥ መገንዘቡ ይጠቅማል:: በዚች አገር ከህዝቡ 85% ገበሬ ነው:: በስተደቡብ ሜዳማ አካባቢ ሲሆን፣ ጥጥና ስኳር ድንች የሚበቀልበት አካባቢ ነው:: በተጨማሪም በዚሁ በስተደቡብ እጅግ በርካታ ሥፍራዎች፣ ረገረግ የሆኑ አካባቢዎች ይገኙበታል በሃገሪቱም በስተሰሜን ጠፍ እንደዚሁ ሜዳማ አካባቢዎች ይገናሉ በዚህ ደግሞ የህዝቡ ዋና መተዳደሪያ ከብት እርባታ ሆና እናገኛለን::

የአፍጋኒስታን አብዛኛው ክፍል ተራራማ ሲሆን አብዛኛው ገበሬ የሚኖረው በተራራማው አካባቢ በሚገኙ ሸለቆዎችና ሸንተረሮች ነው:: የመሬት ይዞታና አከፋፈል እንደ ክፍለ ሃገሩ ይለያያል:: በአጠቃላይ ግን በስተሰሜን በኩል ሰፋፊ መሬቶች በግል ሲያዙ በስተ ደቡብ ደግሞ መሬት በመንደር፣ወይም በጐሣዎች በጋራ የተያዘ ነው::

በ1979ዓ.ም. ታሪኪ መፈንቀለ መንግሥት ሲያደርጉ በሳቸው የሚመራው ኮሚኒስት ፓርቲ የመሬት ይዞታ ማሻሻያ አዋጅ አወጀ:: ግን ብዙ ሳይቆይ ይሸ አዋጅ ውድቅ ሆነ:: የአዋጁ መሠረታዊ ዓላማ በመአከላዊ ክፍለ ሃገራት ያሉት ሃዛራ የተባሉት ህዝቦች የሚኖረባቸውን መሬቶች ለማከፋፈል ነበር:: እነዚህ ህዝቦች በከፊል ዘላን በመሆናቸው መአከላዊው መንግሥት አዋጁን ሲያወጣ "ምን ያስባሉ?" ብሎ አልጠየቀም:: በመሆኑም ይህ አዋጅ የህዝቡን ባህላዊ ኑሮ አናጋው:: በዚህም የተነሳ ከፍተኛ ተቃውሞ ተነሳ:: ይህ የሙድጃሂዶች

አመጽና ያስከተለው ጦርነት ብዙ ህዝብ በስደተኛነት እንዲፈለስ አደረገው:: ድሃ ገበሬዎች በዚያው በአገሩ ውስጥ ትግሉን በመቀጠል በየተራራውና ሸለቆው ተሠማሩ::በተለይ በሰሜን ምሥራቅ የሚገኙ ሃብት ያላቸው ገበሬዎች ደግሞ ወደ ፖኪስታን ተወስደው ከዚያ ትግላቸውን ጀመሩ::

ባጥሩ በአፍጋኒስታን አገር በኮሚኒስት ፖርቲው ላይ ህዝቡን እንዲነሳ የገፋፋው ይህ የመሬት አዋጅ መሆኑ ግልጽ ነው:: ሶቭየት ህብረት በ1979ዓ.ም. መጨረሻ ላይ በወታደር ኃይል በአፍጋኒስታን የውስጥ ጉዳይ እንድትገባ ያደረገ ደግሞ የዚህ የገበሬ አመጽ እያየለ መሄድ ነው::

በ1985 ዓ.ም. እኔ የምሠራበት የእርዳታ ማህበር ጦርነቱ በሚካሄድባቸው በሰሜንና በመካከላዊ አፍጋኒስታን ክ/ሀገሮች ፕሮግራሙን ጀመረ:: በዚህ አካባቢ ምርት ወይም፣ ኢኮኖሚው ተንኮታኩቶ፣ የመገናኛ መንገዶች ፈራርሰው ይገኙ ነበር:: በኛ ግምት ገበሬዎችን መርዳት የሚቻለው እዛው ሀገር ውስጥ ለቀሩት በዚያው በመንደራቸው እንዳሉ የእርሻ መሣሪያ እንደገና እንዲያገኙ በማድረግ ነው ብለን አመንን:: ስለዚህ አዳዲስ የማከፋፈያ ተቋሞችን ዘረጋን፣ ትናንሽ ሱቆች በብዙ ቦታዎች እንዲከፈቱ አደረግን:: በነዚህም አማካኝነት ገበሬዎች በተለይ ለዘር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ማግኘትና ሥራቸውን መሥራት ጀመሩ::

ዛሬ ምንም እንኳን በመንግሥትና በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል የተጀመረው ድርድር ገና የተጠበቀውን ፍሬ ባይሰጥም ገበሬዎች ቀስ በቀስ ወደ መሬታቸው መመለስ ጀምረዋል:: የታጠቁ ቡድኖች ቀስ በቀስ ሰላም በሚፈልገው ገበሬ እየተገለሉ ናቸው:: እንዲያውም በብዙ ቦታዎች ገበሬው ከዚህ በፊት ያደርግ እንደነበረው ለሙጃሂዶች አሥራት መክፈሉን እያቋረጠ ነው::

በኔ ግምት በዚች አገር ሰላም ሊገኝ የሚችለው የእርሻ ምርት እንደገና እንዲንቀሳቀስ በማድረግና ስደተኞች በመጡበት እንዲመለሱ በመርዳት ነው ብዬ እገምታለሁ::

3. የፖላንድ ምሳሌ፣

አቶ ፒተር ዳብሮውስኪ የሶሊዳርቲ የገበሬ ክፍል መሪ

ለገበሬዎች ማስተማመና መስጠት የሚቻለው ለሚያርሱት ሰዎች መሬትን በባለቤትነት በመስጠት ነው ብዬ አምናለሁ:: ይህ የመጀመሪያውና መሠረታዊው ነገር ይመስለኛል:: ለማንኛውም የገበሬው ዋና ጥያቄ ይኸ ነው::

ምክንያቱስ? እርሻ ሲታሰብ መታየት ያለበት ከረዥም ጊዜ አንጻር ነው:: ብዙ ጊዜ የሚመረኮዘው መሠረታዊ በሆነው በቤተሰብ ህዋስነት ነው:: እንደዚህም በመሆኑ የመሬት ይዞታ ማሻሻል የግል ሃብትን የሚያጠናክር ፖሊሲ መሆን አለበት:: በተጨማሪም የአካባቢውን ልምድና ባህልም ማክበር አለበት::

ከዚህ በኋላ ደግሞ መንግሥት አጠቃላይ የሆነ የእርሻ ፖሊሲ ማውጣት ይኖርበታል:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እንከተል የነበረው የኮሙኒስት ሥርዐት ሲሆን በትእዛዝ የሚንቀሳቀስ ኢኮኖሚ ነበረን:: ይህም የማይቀረውን የእጥረትና ችግር አስከተለ::ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሃገሪቱ ወደ ነጻ ገበያና ነጻ ለውውጥ ኢኮኖሚ እየገባች ነው:: ግን ይህ አዲስ ሁኔታ ግልጽና የተቀነባበረ የእርሻ ፖሊሲ አስፈላጊ መሆኑን ሊያስረሳን አይችልም::

ይህ ፖሊሲ የተሳካ ውጤት እንዲያመጣ ከተፈለገ ብዙ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው በመጀመሪያ የገጠሩ ዓለም በፖርላሜንት በደንብ መወከል ይኖርበታል::ገበሬው ከልቡ የሚሠራውና የከተማውም ህዝብ ከገጠር የሚፈልገውን ምርት እንዲያገኝ ከተፈለገ የገበሬ ተወካዮች ፖሊሲው በሚነደፍበት ጊዜ ሃሳባቸውን፣ የገበሬውን ፍላጐት ለማብራራት መቻል አለባቸው::

ሁለተኛ እነዚህን ፖሊሲዎች ከሥራ ላይ ለማዋል በቂ የሰው ጉልበትና የገንዘብ አቅም ያለው የእርሻ ሚኒስቴር መቋቋም ይኖርበታል:: በዚህ መልክ የእርሻው ፖሊሲ ሥነ ሥርዓት ባለው ሁኔታ ካልተሠራ ከቀድሞው ወደ አዲሱ የሚደረገው ሽግግር የተዘበራረቀ ሊሆን ይችላል:: ይህ ሊፈጥር የሚችለው ችግር ደግሞ ገበሬውን ተስፋ ሊያስቆርጠው ይችላል::

ሶስተኛ የገበሬዎች የሙያ ማህበራት በየደረጃው መቋቋምና መጠናከር ይኖርባቸዋል:: እነዚህም የአገልግሎት ማህበራትን፣ የኢኮኖሚና የንግድ ማህበራትን መልክ ሊይዙ ይችላሉ:: እነዚህ ተጠናክረው ሲገኙ በህብረተሰቡ ውስጥ ሚናቸው የዚያኑ ያህል ይጨምራል:: ሚናቸው ከፍተኛ ከሆነ ደግሞ ፖሊሲዎችን ወደገበሬው ለማስተላለፍም ሆነ ለገበሬው የማይመቹ ፖሊሲዎችን ለመቃወምና ለማስለወጥ የተሻለ እድል ይኖራቸዋል::

አራተኛ እነዚህ ፖሊሲዎች ፍሬያማ የሚሆኑት በገበሬውና በአስተዳደሩ መካከል የማያቋርጥ ውይይትና ሃሳብ መለዋወጥ ሲኖር ነው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ የገበሬ የሙያ ማህበራት በህዝብ መገናኛ ዘዴዎች መጠቀም የሚችሉበት ዘዴ ማግኘቱ እጅግ ጠቃሚ ነው ብዬ አምናለሁ:: እንደዚህ ከሆነ አለመግባባቶች ሊወገዱ ይችላሉ:: በተለይ ደግሞ በአምራችና በሸማች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉትን ግጭቶች በመወያየትና በመግባባት ለመፍታት የሚቻልባቸው መድረኮች ይፈጠራሉ ብዬ እገምታለሁ::

አምስተኛው ቅድመ ሁኔታ ወጣቶችን የሚመለከት ነው:: ወጣቶች የሃላፊነት ቦታ እንዲይዙ ማበረታታት ያስፈልጋል:: ዛሬ በያለበት የሃላፊነት ቦታዎች ሁሉ የተያዙት በሶሊዳሪቲ የትግል ዘመን ግንባር ቀደም ሆነው ይታገሉ የነበሩ ሰዎች ናቸው:: እነዚህ ሰዎች የራሳቸውና ዝግ የሆነ "የታጋዮች ጉተ"መፍጠር የለባቸውም:: ወጣቶችን እየቀሰቀሱ እያበረታቱ ወደ ሃላፊነት ማምጣት አስፈላጊ ነው::

መጨረሻም ከውጭው ዓለም የመገናኘቱ ጉዳይ አለ:: ከፍተኛ ለውጦች ሲያደርጉ ብዙውን ጊዜ ህብረተሰቦች ከውጭው ዓለም የመዘጋት አዝማሚያ ይታይባቸዋል:: ይህንን መዋጋት ያስፈልጋል:: ከውጭው ዓለም ጋር ግንኙነት ማስፋት የሀገርንም ሁኔታ ይበልጥ ሚዛናዊ በሆነ መልክ ለመመልከት ይረዳል:: ከዚህ አንጻር በተለይ ከመንግሥት ውጭ የሆኑ ድርጅቶች /ኤንጂኦስ/ ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች በጣም ጠቃሚ ይመስሉኛል::

ዛሬ በፖላንድ በመካሄድ ላይ ያለው ለውጥ ምንም እንኳን ሰላማዊ ለውጥ ቢሆንም አብዮት ተብሎ ሊጠራ የሚችል ነው:: ይህ ሂደት እንዲሳካ ከተፈለገ በተለይ ደግሞ ገበሬዎች በሙሉ ልብ እንዲያመርቱ ከተፈለገ በተቻለ መጠን አርቆ ማየት፣ ስለ ሂደቱ ዓላማና ችግሮች ለህዝቡ ያለማቋረጥ ማስረዳት፣ በተለይ ደግሞ ብዙውን ጊዜ ከሚረሳው ከገጠሩ ዓለም ጋር ያልተቋረጠ ውይይት ማካሄድ ያስፈልጋል::

የፖሳገድ ልምድ የሚያሳየው ሌላም ነገር አለ፡፡ የእርሻ ፖሊሲን መንደፍ በጣም አስቸጋሪ ሥራ ነው፡፡ አብዮት በሚካሄድበት ወቅት አዲሶቹ ባለሥልጣኖች በፍጥነት መራመድ ይገደዳሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ውስብስብ የሆኑትን ነገሮች ቀላል አድርጉ ለማየትና ለውስብስብ ችግሮች ቀላል መፍትሄዎችን ለመስጠት ይሞክራሉ፡፡ የመሬት ይዞታ ጥያቄ የትም ምንግዜም ውስብስብ መሆኑ እየታወቀ ለዚህ ጥያቄ ቀላልና አንድ ወጥ የሆነ መልስ መስጠት አይቻልም፡፡ ነገሮችን ከረዥም ጊዜ አንጻር በማየትና ተገቢ ፖሊሲያችን ለማውጣት ደግሞ ሰላም ያስፈልጋል፡፡